ቁጥር ______________________

ቀን __________________

ለሐረሪ ህ/ብ/ክ/መ/ ፕሬዘዳንት ጽ/ቤት

ለሐረሪ ህ/ብ/ክ/መንግስት ትምህርት ቢሮ

ሐረር

ጉዳዩ፡- የትምህርት ሚኒስቴር በትምህርት ተቋማት የአምልኮ ስርዓትን በሚመለከት ያወጣውን መመሪያ ይመለከታል

ከዚህ በፊት የትምህርት ሚኒስቴር በትምህርት ተቋማት የአምልኮ ስርዓትን በሚመለከት ያወጣውን መመሪያ አስተያየት እንድንሰጥበት ከክልሉ የትምህርት ቢሮ በደብዳቤ ቁጥር 2/1-107/ሥሐከ-21/35 ተጠይቀን አስተያየታችንን በደብዳቤ ቁጥር ሐ/እ/ጉ/823/99 በቀን 05/8/99 መግለጻችን ይታወሳል፡፡

ሆኖም ግን አሁንም መመሪያው ከበፊቱ ባልተሸለ መልኩ በመውጣቱ የህዝባችንን የቁጣ ስሜት ከመቀሰም በላይ መመሪያው አገራችን የጀመረችውን መልካም ራዕይ እና ብሩህ ተስፋ የሚያጨልም እንዲሁም በሙስሊሙ ህብረተሰብ ላይ ከባድ አደጋን ያዘለ በመሆኑ የሐረሪ ክልል እስልምና ጉዳዮች ለጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የክልሉ የእስልምና ሀይማኖት መሪዎች(ኢማሞች)፤የክልሉ እስልምና ጉዳዮች ተወካዮች፤ከየመስጅዱ የተወከሉ የሀይማኖቱ ተወካዮች እና የህግ ባለሙያዎችን ያካተተ አንድ ኮሚቴ አቋቁሞ ረቂቅ መመሪያውን ከህገ-መንግስቱ እና ከሀገሪቱ የትምህርት ፖሊሲ አኳያ አንድ በአንድ በመመርመር ከሰፊው የሙስሊሙ ህብረተሰብ ጋር ከተወያየ በኃላ ይህንን የአቋም መግለጫ ከመፍትሄ ሀሳቦች ጋር አውጥቷል፡፡ ስለዚህ የሐረሪ ህ/ብ/ክ/መንግስት እና የክልሉ ትምህርት ቢሮ እንዲሁም ይህን ደብዳቤ በግልባጭ ያደረስንላችሁ መስሪያቤቶች ረቂቅ መመሪያው አሁን ባለበት ሁኔታ እንዳይጸድቅ የበኩላችሁን አስተዋጽኦ እንድታበረክቱ በአሏህ ስም አበክረን እንጠይቃለን፡፡

‹‹ ከሰላምታ ጋር››

ግልባጭ፡-

- ለጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት
- ለኢ.ፌ.ድ.ሪ. ትምህርት ሚኒስቴር
- ለምስራቅ ኦሮሚያ መስተዳድር ጽ/ቤት
- ለድሬደዋ አስተዳድር ካውንስል ከንቲባ ጽ/ቤት
- ለድሬደዋ አስተዳድር ካውንስል የእስልምና ጉዳዮች ጽ/ቤት
- ለምስራቅ ኦሮሚያ የእስልምና ጉዳዮች ጽ/ቤት
- ለምስራቅ ኦሮሚያ ዞን ትምህርት ቢሮ
- ለድሬደዋ አስተዳድር ካውንስል ትምህርት ቢሮ

ባሉበት

## የትምህርት ሚኒስቴር በትምህርት ተቋማት የአምልኮ ስርዓትን በሚመለከት የወጣ የአቋም መግለጫ

በሀገራችን ኢትዮጵያ ካለፉት ታላላቅ ታሪኮች ውስጥ የነቢዩ መሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ባልደረቦች እስልምና ሀይማኖትን በመቀበላቸው ምክንያት በሀገራቸው በሰላም መኖር አቅቷቸው በተሰደዱ ወቅት ሀገራችን ኢትዮጵያ ብቸኛ መጠጊያ ሆና መመረጧ ብቻ ሳይሆን በወቅቱ የነበሩት ታላቅ መሪ አህመደ ነጃሺ ለስደተኞቹ ያደረጉት እጅግ መልካም አቀባበል በዓለም አቀፍ ደረጃ በተለይም በሙስሊሙ ዓለም ትልቅ ታሪክ ሆኖ ሁሌም ሲወሳ ይኖራል፡፡

ሆኖም ግን የሁሉንም እምነት ተከታዮች በእኩል ለመመልከት ተራራን የመግፋት ያህል በከበዳቸው ቀደምት መሪዎች ምክንያት ከሀገሪቱ ዜጎች በቁጥራቸው ከግማሽ በላይ የሆኑት ሙስሊሞች በገዛ በሀገራቸው እንደ ሁለተኛና ሦስተኛ ዜጋ ተቆጥረው ለረጅም ዘመናት ከማንኛውም የሀገሪቱ የኢኮኖሚ፤የማህበራዊ እና የፖለቲካ ህይወት ውስጥ እንዳይሳተፉ ተገድበው ቆይተዋል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከ1983 ድል በኋላ የብሄር ብሄረሰቦች መብት በህገ-መንግስት ደረጃ ተደነገገ፡፡ የሃይማኖቶች እኩልነትና ነፃነት ታወጀ፤ አዲስ ህገ-መንግስት ፀደቀ፤ ሁሉም የኢትዮጲያ ሕዝቦች በጋራ አጨበጨቡለት፤ የነበረው ተለወጠ፡፡ በእርግጥ ህገ-መንግስታችን ተለውጧል፤ የብዙዎች አዕምሮ ግን አልተለወጠም፡፡ እንደ ቀድሞው ዘመን አጋጣሚ እየፈለጉ ሙስሊሞችን መርገጥ፣ በተቻላቸው ዘዴ ሁሉ በመጠቀም ሙስሊሞችን ከትምህርት ለማራቅ እና ከተሳካላቸውም ያረጀውንና ያፈጀውን ዓይነት ስርዓት ለማምጣት ቀን ከሌት የሚጥሩ ግለሰቦችና ቡድኖች አልታጡም፡፡

በአሁኑ ሰዓት ሁሉም የሀገሪቱ ዜጋ በአዲሱ ሚሊኒየም ብሩህ ተስፋን ሰንቆ ያለ ብሄርና ሀይማኖት ልዩነት እጅ ለእጅ በመያያዝ፤ በመቻቻል፤በመከባበርና በመደጋገፍ መንግስት በነደፋቸው ፖሊሲዎች በንቃት በመሳተፍ በሀገራችን ላይ ሰላምና ፈጣን እድገትን ለማስመዝገብ ሁሉም በያለበት ደፋቀና እያለ ይገኛል፡፡ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ሙስሊሙ ህብረተሰብ እየተጫወተ ያለው ሚና እጅግ በጣም ጉልህ መሆኑ ደግሞ ከማንም የተደበቀ አይደለም፡፡ ሕገ-መንግስታችንም በግልፅ እንደሚያስቀምጠው ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በሀገሪቱ በሚወጡ ፖሊሲዎች እኩል ተሳታፊ እና በውጤቱም እኩል ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ነው፡፡

በተለይም ትምህርት ከሀይማኖት አድሎአዊነት የፀዳ መሆን አለበት በሚል ፖሊሲ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ሙስሊሞችም እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ለዚህ መብት ተጠቃሚ በመሆን አገራቸውንና ህዝባቸውን በማንኛውም መልኩ ለማሳደግ ቆርጠው ተነስተዋል፡፡

የሙስሊሙ ቁጥር ከሀገሪቱ ህዝብ ከግማሽ በላይ ቢሆንም እንኳን በዩኒቨርስቲዎች ያለው የትምህርት ተሳትፎ ከ10 እስከ 14 በመቶ የበለጠ አይደለም፡፡ ይህን በቀድሞ ሥርዓት ተፅዕኖ ምክንያት የተዛባውን የሙስሊሙን የትምህርት ሁኔታ ለማሳደግና ለማሻሻል አዎንታዊ እርምጃዎች ከመንግስት ይጠበቅ ነበር፡፡

ሆኖም ግን በቅርቡ በትምህርት ሚኒስቴር “በትምህርት ተቋማት የአምልኮ ስርዓትን በሚመለከት የወጣ መመሪያ” በሚል ርዕስ የወጣው ረቂቅ መመሪያ በተለይ ሙስሊሙን ህብረተሰብ በእጅጉ አሳስቦት ይገኛል። መመሪያው አገራችን የጀመረችውን መልካም ራዕይ እና ብሩህ ተስፋ የሚያጨልም ከመሆኑም በላይ በሙስሊሙ ህብረተሰብ ላይ ከባድ አደጋን ያዘለ በመሆኑ የሐረሪ ክልል እስልምና ጉዳዮች ለጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የክልሉ የእስልምና ሀይማኖት መሪዎች(ኢማሞች)፤የክልሉ እስልምና ጉዳዮች ተወካዮች፤ከየመስጅዱ የተወከሉ የሀይማኖቱ ተወካዮች እና የህግ ባለሙያዎችን ያካተተ አንድ ኮሚቴ አቋቁሞ ረቂቅ መመሪያውን ከህገ-መንግስቱ እና ከሀገሪቱ የትምህርት ፖሊሲ አኳያ አንድ በአንድ በመመርመር ከሰፊው የሙስሊሙ ህብረተሰብ ጋር ከተወያየ በኃላ ይህንን የአቋም መግለጫ ከመፍትሄ ሀሳቦች ጋር አውጥቷል። ስለዚህ የሐረሪ ህ/ብ/ክ/መንግስት እና የክልሉ ትምህርት ቢሮ እንዲሁም ይህን ደብዳቤ በግልባጭ ያደረስንላችሁ መስሪያቤቶች ረቂቅ መመሪያው አሁን ባለበት ሁኔታ እንዳይጸድቅ የበኩላችሁን አስተዋጽኦ እንድታበረክቱ በአሏህ ስም ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

ረቂቅ መመሪያውን ስንገመግመው ፡-

1ኛ) በዜጎች መካከል ልዩነት ላለመፍጠር በሚል ሽፋን የህገ-መንግስቱ አንቀጾች (አንቀጽ 25፤27፤ 90(2)) እና ከትምህርት ስልጠና ፖሊሲ የጠቀሰውን ነጥብ(2.2.7) አጣሞ በመተርጎም፤

ህገ-መንግስታችን ለሀገሪቱ ዜጎች ያረጋገጠውንና እጅግ መሰረታዊ የሆነውን የሀይማኖት ነጻነት (አንቀጽ 27) ሙሉ በሙሉ የሚጻረር፣

2ኛ) ሁሉም ሀይማኖቶች የራሳቸው የሆነ ሀይማኖታዊ መመሪያዎች(ቁርአን፤ሀዲስ፤እና መፅሀፍ ቅዱስ) ያሏቸው ሆኖ እያለ ትምህርት ሚኒስቴር የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ሀላፊነት ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 471/98 ከተሰጠው ስልጣንና ሀላፊነት ውጭ በምንም መልኩ የማይመለከተውን የአምልኮ ስርዓት መመሪያ ለማውጣት መሞከሩ በራሱ መሰረት አልባ ከመሆኑም በላይ መንግስት በሀይማኖቶች ጣልቃ አይገባም ሀይማኖቶችም በመንግስት ጣልቃ አይገቡም የሚለውን ህገ-መንግስታዊ መርህ በግልፅ የሚቃረን፤

3ኛ) መመሪያው ጸድቆ በማንኛውም በሀገሪቱ በሚገኙ የመንግስትና መንግስታዊ ባልሆኑ፤በህዝብ ወይም በግል በሚተዳደሩ የመዋለ ህፃናት፤የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች፤ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች በተማሪዎች፤በመምህራንና በአስተዳደር ሰራተኞች ተግባራዊ እንዲሆን መታሰቡ አሁን ያለውን ብቻ ሳይሆን ለወደፊት የሚመጣውንም ትውልድ ሀይማኖት አልባ ለማድረግ የታሰበ፤

4ኛ) ስለ ሴኩላራዊ አስተዳደርና ሴኩላራዊ የትምህርት አሰጣጥ የተሳሳተ ግንዛቤን የያዘ፤በሀገሪቱ እየተሰራበት ያለውን የሴኩላሪዝም አተረጓጎምም ሆነ የሌሎችን አገሮችና ታዋቂ የትምህርት ተቋማት ተሞክሮ ለመከተል ያልፈለገ፤

5ኛ) በዝርዝር ባስቀመጣቸው አብይ ጉዳዮች ላይ ማለትም የአለባበስ፤የአምልኮ እና የአመጋገብ እደዚሁም የትምህርት የጊዜ ሰሌዳ በተመለከተ የሙስሊሙን ህብረተሰብ ሀይማኖታዊ ግዴታ እና ልዩ የጾሎት ባህሪ ከግምት ውስጥ ያላስገባ፤

6ኛ) ከሙስሊምነትህ/ሽ አልያም ከትምህርትህ/ሽ በማለት አንዱን የሚያስመርጥ፤

7ኛ) በተለያዩ የሀገራችን ሀይማኖቶች መካከል ለረጅም ጊዜ የቆየውን የመቻቻል ባህል ሙሉ በሙሉ የሚያደፈርስ፤ሰላምን አምጭ ሳይሆን ላልተፈለገ ግጭት የሚዳርግ፤ ጥላቻን የሚያዳብር፤በመንግስትና በሙስሊሞች መካከል አለመተማመንን የሚፈጥር፤

8ኛ) መመሪያው ሙስሊም ባልሆኑ የሀገራችን ዜጎች ላይ ያለውን አሉታዊ ተፅዕኖ በተመለከተ አስተያየት ለመስጠት ባይዳዳንም በአጠቃላይ ይዘቱ እና አላማው የሁሉንም ሙስሊሙ ህብረተሰብ የሀይማኖት ነጻነት የሚጋፋ፤ሀገራዊ ማንነቱን ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ፤ሙስሊሙ ህብረተሰብ በአገሩ ማንኛውም ጉዳዮች ላይ ሙሉ ተሳታፊ ለመሆን እያደረገ ያለውን ጥረት የሚያመክን፤

9ኛ) አገሪቱ እውን ለማድረግ እየጣረች ባለው የዜጎች የሰብዓዊ መብት መከበር፤የዲሞክራሲያዊ ባህል እና የመልካም አስተዳድር መዳበር ላይ ከባድ እንቅፋት የሚሆን መመሪያ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመሆኑም ከላይ ከጠቀስናቸው ነጥቦች አኳያ የሚከተሉትን የመፍትሄ ሀሳቦችና አስፈላጊ ማስተካከያዎችን የሚመለከተው አካል ሁሉ በአፋጣኝ እንዲወስድ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡-

1) መመሪያውን አሁን ባለበት መልኩ የማንቀበለው መሆኑን እየገለጽን በህገ-መንግስታችን አንቀጽ 27/1/ የተሰጠንን ሙሉ የእምነት ነፃነት ማለትም ‹‹ *ማንኛውም ሰው የማሰብ የህሊና እና የሀይማኖት ነጻነት አለው፡፡ ይህ መብት ማንኛውም ሰው የመረጠውን ሀይማኖት/እምነት/ የመያዝ/የመቀበል/፤ ሀይማኖቱንና እምነቱን በግልም በቡድንም በይፋ የማምለክ፤ የመስበክ፤ የመተግበር ወዘተ. መብትን ያካትታል*›› ይህ የዜጎች ህገ-መንግስታዊ መብት በየትኛውም ቦታና ጊዜ ያለመሸራረፍ ሊከበርልን ይገባል፤ይህንን እና ሌሎች ህገ-መንግስታዊ መብቶቻችንን በማንኛውም መልኩ ሊገድብ ወይም ሊጥስ የሚፈልግን አካል ደግሞ በህጋዊ መንገድ እንቃወመዋለን፡፡

2) ረቂቁ ባነሳቸው ዋና ዋና ጉዳዮች የመማር ማስተማሩ ሂደት የተሻለ ይሆን ዘንድ፡-

   ሀ/ አምልኮን በተመለከተ በሌሎች አገሮች እንዳለው በሁሉም የትምህርት ተቋማት ለሙስሊሞችና ለክርስቲያኖች ለየራሳቸው የትምህርት አሰጣጡን በማያውክ መልኩ በህብረት የሚያመልኩባቸው ቦታወች እንዲዘጋጁና ሁሉም አማኝ በነዚሁ ቦታዎች ብቻ እንዲጠቀም ሁኔታዎች እንዲመቻቹ፤

   ለ/ ምግብን በተመለከተ ለሙስሊሙም ሆነ ለክርስቲያኑ ሀይማኖቱ በሚያዘው መሰረት እንዲዘጋጅና ለሁለቱም በየሀይማኖታቸው የተለየ የመመገቢያ ቦታ እንዲኖራቸው፤እንዲሁም ለረመዳን ጾም ጊዜ የሙስሊሙን ሀይማኖታዊ ግዴታ ከግምት ውስጥ ያስገባ ልዩ ፕሮግራም በሁሉም ተቋማት እንዲዘጋጅ፤

   ሐ/ አለባበስን በተመለከተ ሀይማኖታዊ አለባበሶች ምንም ገደብ ሳይደረግባቸው ይልቁንም ጾታዊ ስሜትን የሚቀሰቅሱ እራቁት ከመሆን ብዙም ያልዘለሉ አለባበሶች እንዳይኖሩ በሚያስችል መልኩ መመሪያው እንዲስተካከል፤

   መ/ የትምህርት የጊዜ ሰሌዳ ደግሞ በሁሉም የትምህርት ተቋማት ሀይማኖታዊ ግዴታዎችን ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ በመመሪያው ውስጥ ይካተት፤ይህ መደረጉ ከሌሎች ሀገሮች ተሞክሮ እንደታየው የትምህርት አሰጣጡን በተሻለ መልኩ ለማስሄድ የሚያስችል ከመሆኑም

በተጨማሪ መተሳሰብን እና ህብር፤ክብር፤ፍቅር የሚለውን ጽንሰ-ሀሳብ በትክክል ለማንፀባረቅ ያስችላል፡፡

3) የቀድሞውን የአፄ ስርአት ናፋቂዎች ኢትዮጵያ የበርካታ ብሄርና ብሔረሰብ እንዲሁም ሃይማኖት ተከታዩች አገር የምትሆነው በቃል ወይም በጽሁፍ ብቻ ሳይሆን በተጨባጭ መሆኑንም እንዲገነዘቡ እንሻለን፡፡ አባቶቻችን በሙስሊምነታቸው ያጧቸውን ሙሉ የመማርም ሆነ በሁሉም ሀገራዊ ጉዳዩች ውስጥ የመሳተፍን መብት ተነፍገው ነበር፡፡ ነገር ግን የአሁኑ ሙስሊም ትውልድ ግፍን የሚሸከምበት ጀርባ የለውም፤ስለዚህ በማንኛውም መልኩ እየተካሄዱ ያሉ ሀይማኖታዊ አድሎዎችን መንግስት በትኩረት በመከታተል አድሎን በሚፈጽሙ ግለሰቦች/ቡድኖች ላይ የማያዳግም እርምጃ እንዲወስድባቸውና የፈጠራ ወሬን በማናፈስ ህዝብን ከህዝብ እና ከመንግስት ጋር ለማጋጨት የሚጥሩ የብዙሀን መገናኛዎችን ከእኩይ ተግባራቸው እንዲገቱ መንግስት አስፈላጊውን እርምጃ በአስቸኳይ እንዲወስድ አበክረን እንጠይቃለን፡፡

‹‹ አሏሁ አክበር!! ››